# *የብሔረሰብ ጥያቄ ትናንት፤ ዛሬና፤ የአብሮነት ቀመር ፍለጋው*

ዩሱፍ ያሲን

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ-EPRP) በፍራንክፈርት ከተማ በ May 14, 2011 - ሚያዚያ 18 ቀን 2003 ዓ.ም) በተደረገው ስብሰባ የተደረገ ንግግር

በወሰጣቸው በርካታ ስብስቦች ያካተቱ ሕብረብሄራዊ መንግሥት ምሥረታ በሦስት ደረጃ በደረጃ በሚከናወኑ ተከታታይ እርምጃዎች ተራማምደው ነው ሕዝቦቹ አንድነታቸውና አብሮነታቸን የሚያረጋገጡት የሚትለውን ትዮሪ ባንድ ወቅት ማንበቤ አስታውሳለሁ።

በእነዚሁ ቅደመ ሆኔታዎች መሠረት፤

<u>አንደኛ</u>፤ በቅድሚያ አንድ ማህበረሰብ ወይም ስብስብ የራሴ ነው ለሚለው ላንድ ሃገር ወይም መንግሥት  ወገንተኛነቱን ያረጋግጣል፤

ቀጥሎ

<u>ሁለተኛ</u>፤ በዚሁ ጆግራፊያዊ አሃድ የተካተቱት ማህበረሰቦች ወይም ስብስቦች ባንድ መንግሥታዊ  ትድድር ሥር አብሮ የመኖር ፍላጎታቸውን ያረጋግጣሉ፤

ቀጥሎ

<u>ሦስተኛ</u>፤ ስብስቦቹ በምን ዓይነት አኗኗር ቀመር አብሮ መኖር እንዳለባቸው ይስማማሉ ይላል እሳቤው፤ በትክክል እስከ አስታወስኩት ድርስ።

በዚሁ ዓይነት ልቅምና ክሽን ባለ እንከን የለሽ አካሄድ የተመሰረተ ሃገር መኖሩን እንጠራጠራለን። በማሕበረሰብ ሳይንስ ላብራቶሪ ካልሆነ በስተቀር። በዚህ መልክ የተመሰረቱ መንግሥታት በሃገሮች ምሥረታ መዛግብት ታሪክ የለም ቢባል ማጋነን አይሆንም። በተግባር የሃገሮች ምስረታ በእነዚህ ሦስት ሂደቶች አልፈው መጠናቀቁ ነው አጠያያቂው።

ሃገሮች በዚህ መልክ አይደረጁምም፤ አይመሰረቱምምም። ባንድ ሃገር የታቀፉ ሕዝቦች ወይም ስብስቦች ባንድ ላይ ጉባኤ ተቀምጠው መክረው ዘክረው፤ ይሁንታቸው ተጠይቀው የመሰረቱት ሃገር የለም ማለት ይቻላል። መንግሥታት አመሰራረታቸው ለየቅል ነው። እነዚህን መመዘኛዎች ደረጃ በደረጃ ወይም እርከን በእርከን አሟልቶ ሃገር የገነባ ወይም መንግሥትን ያደላደለ ሕዝብና መሪ መኖሩን እርግጠኖች አይደለንም። ሃገር ወይም መንግሥት የመሰለ ውስብስብ ያለ ተቋም የመገንባቱና ሕልውናን ማረጋገጡ ሂደትና አካሄዱ

ፊርጀ ብዙ ክንዋኔ ነው። በነገራችን ላይ በአማርኛችን በፈረንጅኛው እስቴትና ጋቨርንመንት ለሚለው ሁለቱም ፅንሰ ሐሳቦች መንግሥት የሚለውን አንድ ስያሜ ነው የምንጠቀመው።

እርግጥ፤ በቅኝ ገዢዎች ተቀፈው የተዋቀሩ ሃገሮች የመጀመሪያ ጀግራፊያዊ ቅርፃቸውን ባንድ በተወሰነ ወቅት ባንድ የቅኝ ገዢዋ ሃገር አዋጅ የሚጠናቀቅ ድርጊት ነው። ለምሳሌ እ.ኤ.አ. በ 1890 ኤርትራ በጣልያን ቅኝ ገዢዎች አንዳንድ ጅግራፊያዊ አሃድ ከኢትዮጵያ አካል ተቆርሳ የተፈጠረችው በሮማ በታወጀ ድንጋጌ ነው። ከቅርብ የምናውቀው የኤርትራን ምሳሌ ወሰድን እንጂ አብዛኛው በቅኝ ገዢዎቹ ቀዶ ጥገና የተበጃጁት ቅኝ ግዛቶች የተመሰረቱትና ያሁኑ ጀግራፊያዊ ቅርፆቻቸው የወሰዱት በዚሁ እወጃ ነው ማለት ይቻላል። ሃገረ እስራኤል በ 1948 የተመሰረተችው በተበባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ ወሳኔ መሰረት ነው። ሌሎች ሃገሮች በመመሥረታቸው ማግሥት የመንግሥታቱን ድርጅት እውቅና ለማረጋገጥ ወደዚያ ይጓዛሉ እንጂ የምሥረታው ይሁንታ ከዓለማቀፉ ሕብረተሰብ አይቸራቸውም።

የተለያዩ ሃግሮች ግንባታ በተለያዩ አካሄዶች ተጠናቅቀዋል። በከፍተኛ ስቆቃና ዋጋ ባስከፈሉ ዉጣ ውረዶች አማካኝነት ሕልውናቸውን ያረጋገጡ መንግሥታቱ በርካታ ናቸው። በ 19ኛ ምዕተ ዓመት በኤውሮፓ የተለያዩ ሕዝቦችን ባንድ መንግሥት ጠለላ ሥር የማጠቃለሉ ሂደት በብዙ ወጣ ወረዶችና መስዋዕትነት የተከናወነ አካሄድ ነው። ብሔራዊው መንግሥት ባንድ በተወሰነ የታሪክ ማጋጠሚያ ብቅ ያለ ተቋም ቢሆንም ቅሉ የአመሰራረቱ አፈፀሞችና አካሄዶች ከቶ አይመሳሰሉም። ላንዳንዱ መንግሥት ምሥረታና ግንባታ ራሳቸውን የቻሉ መንስኤዎችና ነባራዊ ኩነቶች መደርደር ይቻላል።

የኢትዮጵያ ጀግራፊያዊ ቅረፅ በታሪክ ሂደት ሲቀያየርና ሲለዋወጥ እንደመጣ እምብዛም አያከራክርም። ሃገራችን በረዥሙ ታሪኳ ስትስፋና ስትጠብ እንደነበረች ለመረዳት የታሪክ መዛግብት ማገላበጥ አያስፈልግም። ሃገራችን የዛሬዋ ጀግራፊያው ቅርፅ የተጎናፀፈችበት ሂደትም ለሕዝብ ቀርቦ በስምምነት አልተወሰነም። በአብሮነታችን ቀመር ላይ ተመካክረን አላፀደቅነውም። ስለዚህ እኛም በዘመናዊ መንግሥት አመሰራረት ከላይ በተመለከትነው እርከን በእርከን አካሄዶች አላለፍንም፤ እቅጩን ለመናገር።

በኤውሮፓ የሃገራት ምሥረታና ጥቅለላ የተወሰኑ የሃገሪቷ ክፍለ ግዛቶች የላቀ ድርሻ እንደነበራቸው አይካድም። ለምሳሌ ፐራሺያ በጀርመኑ አመሰራረት ከሁሉ የላቀ የማዋሀድ ድርሻ ነበራት። ፔድሞንት በጣልያኑ ብሔራዊው መንግሥት ምሥረታ እንደዚሁ። የተወሰኑ የታሪክ መሪዎች በዚሁ አንድ የማድረጉ አዋሃጅ ሂደት ስማቸው ሲጠቀስ እንሰማለን። ለምሳሌ የኦቶ ቮን ቢስማርክ ስም ከጀርመኑ፤ የጋሪባልዲ ስም ደግሞ ከጣልያኑ አንድ የማደረጉ ተግባር ጋር ተያይዞ ሲነሳ እንሰማለን። በሃገራችንም ለደጉም ለክፉም የአፄ ምኒሊክና የሸዋ ክፍለ ሃገር ስም ከዚሁ ተልእኮ ጋር ተቆራኝቶ መነገሩ አግባብነት ይኖሮዋል። የአፄ ቴዎድሮስና አፄ ዩሃንስ አንድ የማድረጉ ድርሻ በሰሜን ምሥራቅ ኢትዮጵያ ኮር ግዛቶች የዘመነ መሳፍንት መቆራቆስ አስወግዶ አንፃራዊ መረጋጋት

ከመፍጠር የዘለለ ብሔራዊ መንግሥት አደላድሉ ተግባር ላይ ወሳኝ ሚና አለነበረውም ባዮች አሉ።

ኢትዮጵያ ብሔራዊ መንግሥት ምስረታ ታሪክም ከዚሁ አካሄዶች እምብዛም ያፈነገጠ አልነበረም። ሃገራችን ካላይ በተጠቀሱት ሦስቱ እርከን አካሄዶች መቼም አላለፈችም። የ3000 ዓመታት የመንግሥትነት ታሪኳን ማለታችን አይደለም። የዛሬ መቶ ስልሣ ዓመት ገደማ ይቺ ሃገር ዛሬ የምትታውቅበት ቅርፅ በያዘችበት ጊዜ ማለታችን ነው፤ እንጂ። ልክ እንደሌሎቹ ብዙ ወጣ ውረዶችና ዋጋ ተከፍሎ ነው የተመሰረተችው። ልክ እንደሌሎች የተወሰኑ ክፍሎቿ ባንድ የማደርጉ ሂደት ወስጥ ወሳኝ ሚና ተጫውተዋል። ልከ እንደሌሎቹ በስም የሚጠቀሱ መሪዎች ባንድ የማደርጉ ተግባርና ተልእኮ መሪ የተዋናይነት ድርሻ እንደ ነበራቸው የሚካድ አይደለም።

ይህ ያለፈው ብሔራዊ መንግሥት አገነባብ ታሪክ እስከ ዛሬ ያወዛግበናል፤ ያነታርከናል፤ ያተረማምሰናል። አልፎ ተርፎ በዛሬው አብሮነታችን ላይ ጥላውን ያጠላል። ይህው ሂደት የወደፊቱ አብሮ ባንድ መንግሥት ሥር ባንድነት መዝለቃችንና መክረማችን አይሞከሬና አይታሰቤ አድርጎታል ባዮች አሉ ከመሃከላችን። ሰለዚሁም ነው ርእሰ ጉዳዩ አወዛጋቢ የሆነው።

በሀገራችን የብሄርስብ ጥያቄ የተሰኘው ጉዳይ የሚያወሳሰበው ይህንኑ በምስረታወ ዙሪያና፥ ሳቢያ የሚነሱ ጥያቄዎች ናቸው። በሃገራችንም ብሔረሰብ ጥያቄ ተሰኝቶ ከቀደምት ተማሪዎች ማሕበር ጀምሮ እስከ ዛሬ አነጋጋሪ ርእስ ሆኖ ያሿከተው፤ ያናቀረውና ውዝግብ መነሻ በዚሁ ብሔራዊ መንግሥት አመሰራረት ዙሪያ ያጠነጠነው ክርክር ነው። ትናንትም ዛሬም አነጋጋሪና አነታሪኪ ርእሰ ጉዳይ ሆኖ ነው የዘለቀው ከተለያዩ ብሔረሰቦች በመጡት የሥልጣን ኤሊቶች መካከል ጦር ያማዘዘው።

የብሄረሰብ ጉዳይ በኢትዮጵያ ብሔረሰቦች(አመካይ አሰያይም ተድርጎ የተወሰደ) በመንግሥታዊው አደረጃጀት የሚኖራቸው ግንኙኝነትና ቁርኚት ምን መምሰል አለበት የሚለውን ጥያቄ መጠንጠኛ ያደረገ ውዝግብ ነው። ባንድ መንግሥት ሥር እንጠቃለል ወይስ እያንዳንዱ ስብስብ የራሱን እድል በራሱ የመወሰን መብት ታውቆለት የራሱን ሕዝብ እጣ ፋንታ ይወሰን ተበሎ የሚቀርበው ጥያቄ የዚሁ የማንነት ፖለቲካ አመለካከት አንዱ አካል ነው።

ያለፉት የታሪክ ኩነቶች የወደፊቱ አብሮ መኖራችን እድልም ጭምር አጠያያቂ አደርጎታል ባይ ወገኖች አመለካከትም ርእሰ ጉዳዩን ይበልጥ ወሰብስብ አድርጎታል። በሃገራችን የማንነት ፖለቲካ ያስከተለው ብሔርተኛነት መዘዞች በተለያዩ ቅርፆቹ በዚሁ ሥር ማጠቃለል ይቻላል። በካልቸርና በሃይማኖት ዙሪያ የሚጠዙትንም ጭምር።

ዋለልኝ መኮንን የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አራተኛ ዓመት የፖሎቲካል ሳይንስ ተማሪ በነበረበት ወቅት በ 1962 ዓ.ም. "On the Question of Nationalities in Ethiopia በሚለው ርእስ ሥር ያቀርበው ፅሑፍ የውዝግብ መነሻ የሆነውም ይህንኑ ጉዳይ ፊት ለፊት ለመጋፈጥ በመሞከሩ ነው። እስከ ዛሬ በዋለልኝ ወርቀት ላይ የተቀጣጠለው እሰጣ አገባ አላባራም። ሙግቱና ክርክሩ ዛሬም እንደ ተጧጧፈ ናቸው፤ ጎራ ለይቶ። በደጋፊዎቹና በተፃራሪዎቹ መካከል። በሃገራችን የብሔረሰብ ጉዳይ በተነሣ ቁጥር የዋለልኝ መኮነን ስም አብሮ ይነሳል።

ፀሓፊው ወርቀቷን ለውይይት መነሻነት ብቻ እንድታገለግል መፈለጉን አስረግጦ ከይዘቱ (ኮንተክስት) ውጭ እንዳይተረጎምበት በመግቢያው ላይ ያቀረበውን ማሳሳቢያ በግምት እንዳልተወሰደ ግልፅ ነው። ፅሑፉ የብዙ ተቺዎች ኢላማ ሆኖዋል። የተለያዩ ወገኖች በፊና ፊናቸው ወርቀቱን ለራስቸው ፖሎቲካዊ ማረማመጃ መተርጎማቸው አልቀርም። የዋለልኝ ተችዎችና አድናቂዎች፤ ለማቃለል  በሦስት ጎራ ከፍሎ መመልከቱ የሚቻል ይመስለናል።

ፀሐፊውን ዛሬ ለዚሁ ሁላ በኢትዮጵያ ሕዝብ አብሮነት፤ ብሔራዊ አንድነትና ሕልውና ላይ በብሔረሰብ መብት ስም ለተደቀነው አደጋ በቀጥታ ተጠያቂ አድርገው ይመለከቱታል፤ ገሚሶቹ። እነዚህ ክፍሎች አልፎ ተርፎ ወርቀቷን የጣልያን ቅኝ ገዢዎች በ 1928 ከነደፉት የኢትዮጵያ ካርታ ንደፍ ካር የሚወዳደር መርዝ አድረገው ይመለከቱታል። ለዚሁ ይቅር የማይባል ኃጥያት በመቃብሩ ሳይቀር ፀሐፊውን ከመኮነን አይመለሱም፤ እነዚህ ወገኖች። ከዚሁ ውግዘት ዋለልኝ የሚወክለውን ከዚያ ያ ለውጥ ፈላጊ ትውልድ ማንም ነፃ አያወጡም። በጅምላ ተጠያቂዎች ናቸውና በእነሱ እይታ።

ለሁለተኞቹ ደግሞ ዋለልኝና ፅሁፉ አሻጋግረው የመመልከት ራዕይ የሰነቀ ከጊዜው በፊት የተፈጠረ ሓሰብ አፍላቂነት ተምሳሊት ነው። ለእነዚሁ አድናቂዎቹ ራዕዩና መፍትሔ ሓሳቦቹ እንከን ባይወጣላቸውም ወያኔና ሌሎቹ ጠባብ ብሔርተኞች ጉዳዩን አጣመው ለእኩይ ዓላማቸው ማስፈፀሚያ አዋሉት ነው መከራከሪያቸው። ሦስተኛ ወገኖች ደግሞ አሉ። ለእነሱ ደግሞ ዛሬ ወያኔ ኢሕዴአግ የዘረጋውን ፌደራላዊ ሥርዓትና በቋንቋ ላይ የተመረኮዘው አከላለላቸው ምንጩ የዋለለኝ የብሔረሰብ ፅሑፍ ነው። ወያኔ ኢሕዴአግ በ 1983 አዲስ አበባን ለመቆጣጠር ወደ መሃል ሃገር ያቀናው ጥቃት ዘመቻ ዋለልኝ ያሰኙት ያለ ምክንያት አልነበረም። ወያኔ ራሱን እንደ ዋለልኝ ወራሽና አደራ ጠባቂ አድርጎ ለማቅረብ ይሞካክራል። ይዳደዋልም። ልክ ራሱ የሰመጥሪው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ቅርስና ውርስ ጠባቂ ለመሰኘት የሚያደረገው አቀራረብ። የዋለልኝ ጓዶች የሆኑትን እነ ፀጋዬ ደብተራውን አፍኖ ደበዛቸውን ያጠፋ ሃይል መሆኑን ተዘንግቶ። በሌላው በኩል የዚያ ቀደምት የተማሪዎች እያንዳንዱ መሪና አክቲቭስት ሁሉም የራሱን ብሔረሰብ አደራጅተው ለማታገል ባዲስባባ እንገናኝ ብሎ የራሱን ብሔረሰብ ብቻ ነፃ ለማውጣት ለትግል ጫካ የገባ ያስመስላሉ፤ ወያኔዎች። ልክ  እነሱ ትግራይን ለማውጣት እንዳደረጉት።

የኢትዮጵያ ቀደምት ተማሪዎች በመጀመሪያ በሃገርቷ በሰፈነ መሬት ይዞታ በመቃወም መሬት ለአራሹ የሚለውን መፈክር አንግበው በሰላማዊ ሰልፍ ተቃውሟቸውን ገለፁ። የዋለልኝ ፅሑፍ ከመውጣቱ ከሦስት ዓመት በፊት። በሃገራችን ቀደምተ ተማሪዎች አንገበው የተነሱትን ዋና ቁም ነገር የመሬትና የብሔረሰብ ጥያቄ በጣምራ ነበረ ማለት ይቻላል። ሁለቱም የተያያዙ ነበሩ በእነሱ እይታ። በጭሰኛው ሥርዓትና በብሔረሰብ በሚደርሰው በደል መካከል ያለውን የጠበቀ ቁርኚት ለማሳየት። ሁለቱም ከሥር መሠርቱ መለወጥ ነበረባቸው፤ በኢትዮጵያ ዲሞክራሲን በእውን ለማሰፈን ከተፈለገ። በ1965 የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች መሬት ለአራሹ የሚለውን መፈክር አንግበው ሰለማዊ ሰልፍ ወጡ። በዚያን ወቅት ገበሬ ካመረተው እስከ 75 በመቶ ለባለመሬቱ እንዲያስረክብ በሕግ የተደነገገባት ሃገር ነበረች፤ ኢትዮጵያ። ይህንን ግፍ ያለተቃወመ ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብ ከቶ ሊኖረው አይችልም ነበረ። ምንም እንኳን እስከ ዛሬ የመሬት ባለቤትነቱ ጉዳይ ቢያነታርክም የካቲት 1967ቱ ሥር ነቀሉ የደርጉ የመሬት አዋጅ ጭሰኛውን ከዚሁ ክፊያ ነፃ አድርጎታል። የምርቱ ተጠቃሚም አደርጎታል። የኢትዮጵያ ገበሬ ከፈተኛ ድል የተጎናፀበት ክንዋኔ ነበረ፤ የመሬት አዋጁ።

በሌላ በኩል፤ ይህንን የጭሴኛው የመሬት ይዞታ ከሃገራችን ዘመናዊ መንግሥት ምስረታና አገነባብ ሂደት ጋር በቅርብ የተቆራኘ ነው። በተለይም የዛሬ 130 ዓመት ገደማ አፄ ምኒልክ ወደ ምስራቅ፤ ምዕራብና ደቡብ ያደረጓቸውን ድንበር የማስፋፋት ዘመቻዎች ጋር። ምክንያቱ በነዚሁ ዘመቻዎች አማካኝነት ጭምር ነው ሃገራችን የዛሬው ጆግራፊያዊ ቅርፅዋን የተቀዳጀችው። ከሃገራችን አነተራኪ የታሪክ ምዕራፎቹ በግንባር ቀደም የሚጠቀሰው ይኸው ዘመቻና ውጤቶቹን የሚመለከት የታሪካችን ምዕራፍ ነው። የብሔራዊ መንግሥት የመፍጠርና የማደላደል የሚጠይቀውና የሚያስከፍለው ዋጋና ውጤት አድርገው የሚመለከቱ ወገኖች ነበሩ፤ አሁንም አሉ። ፈረንጆቹ ኮላተራል ዳሜጅ የሚሉት ዓይነት፤ አይቀሬ የጎን ጥቃትና የመንግሥትና አወላለድ ምጥ ብቻ።

በአንፃሩ ይህንን የመሰሉ ትረካዎች የማይዋጥላቸው እየተበራከቱ ከመጡ ሰንበትበት ብለዋል። በሁለት ዋና ምክንያቶች። አንደኛው የታሪክ አፃፃፋና የአተራረክ ዘይቤ የታሪክ ተመራማሪዎች ፍተሻ በቅጡ ማለፍ ስለሚያቅተው። ሁለተኛውና ዋነኛው ግን ታሪኩ በድል አድራጊዎቹ መነፅር የተቃኘና የተከሸነ ነው ብለው ስለሚያምኑ። የድል ተደራጊዎቹ የልጅ ልጆች ባንድ ወቅት በሥርዓተ-ትምህርትም ሳይቀር ጭምር የተነገራቸውን ታሪክ ለመቀበል አሻፈረን እያሉ ናቸው። የአጼ ምኒልክ ወደ ምስራቅ፤ ምዕራብና ደቡብ ያደረጓቸውን ዘመቻዎች ባንዳንዶቻችን እይታ ማዕከላዊ መንግሥት ማደላድልና በፅኑ መሰረቶች የማቆም እርምጃዎች ሆኖ ሲታዩ ለአካባቢው ተወላጆች ግን "በቅኝ ግዛትነት" ከመያዝ ያልተለዩ የሃገሬው ሕዝብ ጉልበት መበዝበዝና ጭቆና ሆኖ ይታያሉ። የዘመቻው ኢላማ የነበሩት ሕዝቦች ከቀያቸው ያፈናቀለ፤ መሬታቸውን የቀማ የማስገበር "ወረራዎች" ናቸው ብለው ይመለከቱታል። የሃገሬው ሰው ሰብእናን የደፈሩና ማንነቱን ያዋረዱ ዘመቻዎች ሆነው ይታረካሉ፤ በእነሱ ዘንድ።

ግዛት ማስፋፋት ነው ተባለ፤ ሃገር ማቅናትም አልነው፤ ሥልጣኔና ለአሕዛብ ማዳረስ ተባለ፤ መሰረታዊው ጉዳዩና ወሳኙ መግለጫው የሌላው ዜጋ መሬት መንጠቅ ነው። የመሬቱ ነባር ባለቤቶቹን ከገዛ መሬታቸው ማፈናቀል ነው ውጤቱ። አርመኔውንና አሕዛብን ለወንጌል ብስራት የማዳረስ ተልእኮ ብንሰጠውም ተግባራዊ ውጤቱ ያው አንድ ነው። ከዚያ የሚገኘዋን ቱርፋትና ምርት ለራስ የማድረግ እስከ ነበረ ደረሰ የገበሩት ሰዎች ጉልበታቸው መበዝብዙ አልቀረም። በሌላ ሰው መሬት ላይ ሰው ማስፈር፤ በቦታው ሌላውን አስገብሮ የጉልበቱን ዋጋ ከነጠቀነው በደል ተፈጽሟል። ያለ ጥርጥር። ጉልበት ተበዝብዞዋል። ይህ የማይታበል ሓቅ ነው። ለዚሁ ድርጊት ምክንያቶች መደረደር ይቻል ይሆናል። በዚያኑ ታሪካዊ መጋጠሚያ አስፈላጊ እንደነበረ ተቃራኒ ሙግተቶች መደርደር ይቻላል። ዋለልኝ መኮነንን ያነሳሳው ይህንኑ በደል የማስተካከል የአፍላ ወጣትነት የለውጥ ፍላጎት ነው። የኢትዮጵያ ለውጥ ፈላጊው ትውልድ ለሥር ነቀል ለውጥ ያነሳሳው ይህንኑ ያልተስተካከለ ግንኙኝነት ነው።

እዚህ ላይ አንድ ግልፅ መሆን ያለበት ነጥብ አለ። በእነዚሁ ሁሉ ምክንያቶች ይህ የታሪካችን ምዕራፍ ዛሬም የንትርክ መነሻነቱ አላበቃም። በእነዚሁ ላይ የጋራ ግንዛቤ መገኘቱ የግድ ይላል ታሪካችን የሁላችን አሳባሳቢ ማንነት አካል ሆኖ ለብሄራዊ አንደነታችን ማጎልበት አንድ ራሱን የቻለ ግብዓት ሆኖ ማገልገል ካለበት። ለዚሁም ነው እነዚሁ አነታራኪዎቹ የሃገራችን የታሪክ ምዕራፎች እንደገና መነበብና ትክክለኛ ገጽታቸው መታወቅ ያለበት። በታሪክ ተመራማሪዎች ሁነኛ የታሪክ አጠናና የፍተሻ ዘዴን በመጠቀም።

በሃገራችን የነበረው የብሔረሰብ ጥያቄ ከመሬቱ ባለቤትነትና ከዲሞክራሲ ማስፈን ጋር አያይዘው የተመለከቱት የቀደምቱ የተማሪ ንቅናቄው መሪዎችና የዋለልኝ የትግል ጓዶች ለችገሩ በጣም ቀላል መፍትሔ ነበረ ያቀረቡት፤ ቢያንስ በትዮሪ ደረጃ። ጥያቄው የቅኝ ግዛትነት ይዘት እንዳለው ከተረጋገጠ የራስን እደል በራስ በመወሰኑ ታውቀላቸው ነፃ የራስ መንግሥታት በመቀለስ እልባት ይሰጠዋል ነው፤ አቀራረቡ የነበረው። በሌላ በኩል፤ ጉዳዩ ባንድ ሃገር ባንድ መንግሥት ጠለላ ሥር ሊጠቃለሉ በሚችሉ ሰብሰቦች ጉዳይ ሆኖ የብሔራዊ ጭቆና ይዘት ካለው ግን ባንዱ ወይም በሌላው ያንድ ቅርፅ መንግሥት ሥር በሚደረገው የሥልጣን ድልድል መፍታት አይገድም ነው። ቀለል ያለ አቀራረብ፤ ቀለል ያለ የአፈታት ዘይቤ ነበረ። አሁኑም በትዮሪ ደረጃ። በተገባር ሲታይ ግን እንደዚሁ ቀላል ሆኖ አልተገኘም። እስከ ዛሬ ይህ ጥያቄ መቋጫ አልተበጀለትም። ምን ያህል አስቸጋሪ እንደነበረ እስከ ዛሬ ሁነኛና አስተማማኝ ቀመር አለመገኘቱ ራሱ በቂ ማስረጃ ነው። አሁንም እያወዛገበን፤ እያነተረከን ይገኛል። አብሮነት ቀመርና ፎርሙላ ፈለጋው አሁንም ቀጥሎዋል። የራስን እድል በራስ ለመወሰንና የሕዝቦቻቸውን የራሳቸን መንግሥታት ምሥረታ የሚታገሉ ያንዱ ወይም የሌላው የብሔረሰብ ነፃ አውጪ ግንባሮች በሃገራችን እንዳሉ ናቸው። የብሔረሰብ ጭቆናን እንደ አንድ አታጋይ መፈከር አንገቦ የተነሳው ሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ በአዲሳ አባባ በሥልጣን ከተቆናጠጠ 20 ዓመታት በኋላም ጭምር። ይባስ ተብሎ

የትግራይ ነፃ አውጪ አሁኑም ስሙን አልለወጠም። ዓላማውን መለወጡንም በይፋ የነገረን ነገረ ያለ አይመስለኝም።

እሱ ብቻም አይደለም። ባንድ ትድድር ሥር በአብሮነት ለመጠቅለል ከወሰኑ በኋላም ስብስቦች እንደገና ተቧድነው ይሯከታሉ፤ ከብዙ ሃገሮች ታሪክ እንደምንመለከተው። ማሕበረሰቦች በመንግሥታዊ ጠገጎች አማኻንነት የሥልጣንና ሃብት ድረሻ ድርሻውን ድልድል ምን መመሰል አለበት የሚለው ጉዳይ ልያናቁራቸው እንደምችልም ደጋግመን እንመለከታለን። የሥልጣን ክፍፍል ቀመርና የራስን ዕድል በራስ የመወሰኑ መብትም የዚሁ ፍላጎት ማወቂያና አወሳሰን ማካኒዝም ሆኖ የተተለሙ ዘዴዎች ናቸው።

በሥልጣን ያለው መንግሥትና ገዢው ፓርቲ ቅርብ ጊዜ ወዲህ የብሄረሰብ ብቻ ሳይሆን በተለያዩ እምነት ተከታዮች መካከል የሥልጣን ዕድሜ ማረዘሚያ ካርዶች ሁላ መጠቀም እንደሚችል ተደጋግሞ ተነግሮዋል። ሰሞኑ ከመዘዘው ከአባይ መገደቡና ከዳግም የድንበር ጦርነት ከመለኮሱ በተጨማሪ ሌሎች መተረማመሻ፤ አቅጣጫ ማስለወጫ የቡወዛ ካርዶች እንዳሉት መገንዘብ ያስፈልጋል። ከማስቀየሻዎቹ (የዶር ብርሃኑ ነጋን አባባል ልዋስ መሰለኝ) የመጨረሻይቱን ካርድ ገና አልመዘዘም። በተለያዩ የሃይማኖት አማኞች መካከል ጠብ መጫር እንደሚችል መገንዘቡ ከባድ አይደለም። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የእምነት ቤቶች በእሳት መጋየታቸው ዜና ተደጋግሞ እየተሰማ ነው። የቁዱስ ቁራን መፅሓፍ በሽንት ቤት ተወርውሮ ተገኘ ተብሎ የሚቀጣጠሉ አምባጓሮች እየተበራከቱ ነው። የሚገርመው ግን አንድ ሰው ለዚህ ድርጊት ተይዞ ተገቢውን ቅጣት አገኘ ሲባል አለመስማታችን ነው። ከሁለት ሳምንታት በፊት በአፋር ክልል በአይሣዒታ ከተማ ለሱካር ፖሮጀክቱን የተካለለውን መሬት አወሳሰድ የተቃወሙት ወጣቶችና የሃገር ሽማገሌዎች ለእስር የተዳረጉት ከፖረተስታንቴቹ ጋር የእምነት ግጭት ፈጠራችሁ በሚለው ሰበብ ነው። ግጭቱ አሁንም ተቀጣጠለ የተባለው ቁዱስ ቁራዓንን አንገላታችሁ ነው።

በእምነት ሳቢያ የሚጫሩ ቁሩቁሶች ስሜት ቀስቃሽ በመሆናቸው ስለእነሱ በግልፅ መነጋገሩና ሓሳብ መለዋወጡ አመቺ አይመስልም፤ ለብዙዎቻችን። የሚያስፈራ ታቡ ወይም ስም አይጠሬ ሆነው የሚታየን፤ በዚሁ ምክኒያት ይሆናል። ሰሞኑን በግብጽ ሃገር በእምነት ሳቢያ ለሚደረገው መገዳደል ሲጠቀሱ የምንሰማቸው ምክኒያቶች በጣም አሳፋሪ ናቸው። በዚሁ ምክኒያት ደግሞ አስፈሪም ናቸው። ባልተረጋገጡ አሉባልታዎች ላይ ተመርኩዘው ቤተ እምነቶቹን በእሳት ማጋየቱ ምን ያህል ጥላቻን ማራገብ ቀላል እንደሆነ በአንፃሩ ደግሞ የእምነት ብጥብጥን መቆጣጠር ቁልጭ አድርጎ ያመለክታሉ። በካይሮ ለቤተከርስትያኖቹ በእሳት መጋየት ምክኒያት የሆነቸው አንዲት ያሰለመቸው ክርስትያን ሴት፤ ያለውዴታው በቤተ ክርስቲያኑ መታገቷ ነው። አልፎ አልፎ እንደሚባለው ጉዳዩ የተወገደው የሙባራክ ሥርዓት አብዩቱን ለመቀልበስ የሚደረገው የመጨረሻ መፍጨርጨር ከሆነ ደግሞ ይበልጥኑ ትምህርት ሰጪ ነው፤ ለእኛ። የተወሰኑ ዜጎች ደግሞ ለክርስትያኑ ወገኖቻቸው የአሜሪካን መንግሥት ጥበቃ እየተማፀኑ ናቸው። ይህ ደግሞ ለውጭ ጣልቃ ገብነት በሩን

በርግጾ ይከፍታል። የሊቢያና የየመን መነሳሳቶች ይሰናከለውና ያወሳሰብወም የአካባቢያዊና ዓለማቀፋዊ ጣልቃገብነት መሆኑን አንዘንጋ፤ መግቢያ ቀዳዳ ካገኙ።

በኢትዮጵያችን የብሔረሰብ ብቻ ሳይሆን ሃይማኖትም የውዝግብና የማናቆሪያ መነሻ ሊሆን መቻሉ የብዙዎቻችን ስጋት እየሆነ ከመጣ ሰንበትበት ብሏል። በቂ ፍንጪችና አመልካቾች ብቅ ብቅ እያሉ ናቸው። የምንመለከታቸው ጉንተላዎች ድግሞ በየእለቱ እሳሳቢነታቸው እየጨመረ መጥተዋል። በማስጠንቀቅያ ደወልነታቸው እንወሰዳቸው። ጉዳይ ፈንድቶ ከቁጥጥር በሚወጣበት ማግሥት መፍትሔ ፍለጋ መካለቡ አዋቂነትም ጭምተኛነትም አይደለምና።

በዓለም ደረጃም ሆነ በአካባቢያቸን የሚታየው የእስልምና መነሳሳቶች በኢትዮጵያዊያኑ ሙስሊማዊ ማንነታቸው ላይ ተፅእኖ ማሳደሩ አሌ የማይባል ሓቅ ነው። መንግሥትና ሃይማኖት በቅጡ አለመለየታቸው፤ በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት የሙስሊሙ ወኪል አደረጎ የሚያስቀምጣቸው ግለሰቦችና ተቋማት(መጅሊሳል አዕላ ዓይነቱ) ላይ እምነት ማጣቱ፤ በዜግነት መብቶች በመከበሩ ረገድ የሙስሊሙ ወገን ደግሞ ደጋግሞ የሚያሰማቸው ቅሬታዎች ከቅርበት ተፈትሾ አስተማማኝ መፍትሔ ፍለጋ መኳተን አለበን። እነዚህ የካልቸርና የማንነት ጥያቄዎች በሌላ በኩል ደግሞ በክርስቲያኑ ወገን ከዚህ በፊት "ታሪካዊ ጠላቶቻችን" ብሎ በሚመለከቷቸው ያካባቢ ሃገሮችና ሕዝቦች የስጋት ምንጭነት ምስልን እያጎላ ማምጣቱም አይቀሬ ነው። በእነሱ ዘንድ "የክርስትያን ደሴት" መሻገ ሥነ-ልቦናም ያጠናክራል እንጂ አያላዝበውም። አንዱ ስለሌላው የቀረፅው ምስል ብቻ ሳይሆን የታፈኑ ቁርሾዎች ግልጽና ይፋ የሚወጡት ጠብ በተጫረ ወቅት ላይ ነው በሎ ያስጠነቀቅናል የውዝግብ አጥኒዎቹ። በሊባኖስም ሆነ በሩዋንዳ የተመሰከረው ይህ ነው። በእንጭጩ ሓይ ተብሎ መፍትሔ ሊፈለግለት የሚገባ አንገብጋቢ ጉዳይ ነው።

በመግቢያ የጠቅስኳቸውን ሦስቱ ቅድመሁኔታዊ አካሄዶች ባንከተልም፤ ታሪካችን ያላባሩ ጦርነቶች ታሪክ ቢሆንም ቅሉ የአብሮ መኖሪያ ቀመሮች በታሪክ አጋጣሚዎች ሲፈለጉ ነበረ። የተገኙበት ጊዜም ነበረ። ለዚሁ አለመግባባት ሥልጣንን ባልተማከለ አደረጃጀት መዘርጋት አንዱ ፍቱን ፎርሙላ ነው ተብሎ የታመነበት ፌደራላዊ አደረጃጀት አማራጭ አንዱ ነው።

በረዥሙ ታሪካችን በርካታ የአብሮነትና የማስተሳሰሪያ ስልቶች ሲፈለጉ ነበረ። ልክ እንደ ሌሎቹ ሕዝቦች የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች አንዱ ከሌላው ጋር የነበረው መስተጋቢርም ይህንኑ እውነታን ያመለክታል። የኛዎቹም ልክ እንደሌሎቹ የግጭት፤ አጥር የማጠርና ተደማምጠ፤ ተነጋገሮ በአብሮነት ጎን ለጎን የመኖር ታሪክም አስመስክረዋል። በአመዛኙ ታሪካችን የጦርነት ታሪክ በመሆኑ ስለ ግጭት ቢተርክም ቅሉ የመነጋገርና ተወያይቶ ወደ ስምምነት መድረሱን የተለመደ አሰራርር ነበረን። አሁንም አሉን። አንድነታችና የሃገርጥዋ ሕልውና ለመታደግ ከዚህ በፊት በተለያዩ ሥርዓቶች የተሞከሩ አስተሳሳሪ ሆነው

የሚታዩዋቸው እሳቤዎች ነበሩ። አሁን በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥትም የራሱ አስተሳሳሪ የሚላቸው እሳቤዎች አሉኝ ባይ ነው።

በተለያዩ ሥርዓቶች ምን ምን እንደነበሩ እስቲ ላንድ አፍታ እንመልከታቸው።

በአፄ ሃይለሥላሴ ዘመን የኢትዮጵያ ያስተሳስራሉ አንድነቷን ያጎላብታሉ ተብለው የተገመቱና በእሳቤ የተወሰዱት ዋና ዋና አቀራኝ ግእባቶች

- የዘውድ አገዛዝ ሥርዓት
- ከተለያዩ ብሔረሰቦና አካባቢዎች በተውጣጡ የሥልጣን ኤሊቶችን በአቻ ጋብቻ ድር በማጠላለፍና ማሳተሳሰር፤
- ክርስትና በማንሳትና አንድ ሃይማኖት ተከታዮችን በማብዛት፤
- በትምህርት ሥርዓት አማካኝነት የተወሰኑ እሴቶችና ታሪክና ካለቸር እንዲሰርፅ ማድረግ በግንባር ቀድም የሚጠቀሱ ነበሩ።

በወታደራዊው ደርግ ሥርዓት እይታ ደግሞ፤

- የሠርቶ አደሩ ፓርቲ
- ቀይ ጠር
- የተማከለ መንግሥታዊ አደረጃጀት
- የዓለም አቀፍ ሶይሻሊስታዊው የትግል ትብብር

የኢትዮጵያን አንድነትና የሕዝቦቿ አብሮነት ያደለድላሉ ተብሎ የተገመቱ እሳቤዎች ነበሩ።

በዘመነ ወያኔ-ኢሕአዴግ ደግሞ

- በ አንቀፅ 39 አማካኝነት የመገንጠል መብት ሕገ መንግሥታዊ ዋስትና ማገኘቱ፤
- ሥልጣንን ከማዕከል ወደ ክልሎች የዘረጋው ፌደራላዊ ሥርዓት መመስረቱ የኢትዮጵያ ሕዝቦች በአብሮነታቸው ለማዝለቂ አስተማማኝ ዋስትና ይሰጣሉ ተብሎ የሚታሰቡ ናቸው።

እነዚሁ በጣም አጠር ባለ መንገድ ሦስቱ መንግሥታት ለአብሮነታችን አስተሳሰሪ ዘዴዎች ተደርገው የተወሰዱ ናቸው።

ከዚህ ወጭ ሌሎች ታሳቢዎችም ነበሩ። ክበረ ነገስትን ማዕከል ያደረገ የሰለሞናዊ ሥረው መንግሥት ተረካ ቁርኚት፤ በግራኝ አህመድና በኋላ ላይም በአፄ ዩሃንስ የተሞከረው ኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ የአንድ እምነት ተከታይ ማድረጉ ዘመቻም እንዳንድ አዋሓጅ ማንነት መፈጠሪያ ስልት ተደርጎ ተወስዶ ነበረ። ሁሉም አንድ ከሆነ የሚያነታርከን ልዩነት በማሃላችን አይኖረም ነው ሎጂኩ። በዚያኑ መጠን የሚያወዛግብን ጉዳይ ከቶ ሊኖር አይችልም ነው ግምታቸው። ሌሎችም ሙከራዎች ነበሩ።

የተለያዩ ምሁራን ያቀርቧቸው አብሮነታችን በተደላደሉ መሥራቶች ለማስቀመጥ በአሳቤ ቢወሰዱ ይበጃሉ የተባሉ አሳባሳቢ ማንነት ምርኩዞች አሉ። ጥቅቶች ብቻ ለመጠቃቀስ፤

አንድ የጨነቀው ምሁር ባንድ ወቅት ላይ አዲስ የሰሎሞንና የንግሥት ሳባን ተረታ ተረት(myth) ባዲስ እንደገና መፈብረክ እንደሚያስፈልገን አስመልክቶ ያቀረበው ሓሰብ በዚሁ ጥረት ወስጥ የሚካተት ይሆናል። ቃል በቃል መፈብረክ ነበረ ያለው።

አሳሳቢው እነዚሁ ሁላ ለዘላቂው አብሮነታችን ፍቱን ቀመር ሆነው አለማገልገላቸው ነው። ቁም ነገሩም ትምህርት ሰጭነቱ እሱ ነው። ምክኒያቱ የራስችን መንግሥት ከመቀለስ በመለስ አብሮነታችን መፍትሔ የለውም ባዩች በመካከላችን ዛሬም አሉ። የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት ይታወቅልን ባዩች አሉ። እነዚህ ጥያቄዎች አብሮነታችን ዘላቂና አስተማማኝ መቋጫ አለማገኘቱን ነው የሚያመለኩቱን። ከላይ እንደተመለከትነው አንድነታችን ስጋት ተደቅኖበታል።

ሕዝቦች ባንድ መንግሥት ሥር ባንድነት እንጠቃለል ወይስ እየራስ ራሳችን መንግሥታት እንቀልስ የሚለው ውዝግብ መነሻ ሆኖ ያሻኩታቸዋል። ያሯኩታቸዋል። አመሰቃቃይና አተረማማሽ የብሔርተኛነት ቅርፆች የመከሰቱትም ላንድ ስብስብ የራሱን መንግሥት እንዲኖረው አስፈላጊነትና አላስፈላጊነት ሳቢያ ነው። ለብዙ ብሔርተኛነት ተመራማሪዎች ይህው ነው የብሄርተኛነት እምብርቱና ወሳኝ መግለጫው። ስለዚህ ጥያቄው አሁንም መፍትሔ ይሻል።

በሌላ በኩል፤ ማሕበረሰቦችን የሚያውዛግባቸው በቡድን ቡደን መቧደናቸው አይደለም። ወይም እነዚህ ስብስቦች በተለያዩ የእድገት ደረጃዎች መገኘታቸው ወይም በዚሁ ምክኒያትነት በተለየዩ መጠሪያ ስያሚዎች(የወያኔ ኢህዴአጉ ብሔር፤ ብሔረሰብና ሕዝብ አጠራሮች) መታወቃቸውም አይደለም። ባንድ ቁም ነገር ሳቢያ መነታረካቸው ነው እንጂ። በመንግሥታዊ ጠገኖች በመካከላቸው መኖር ስለሚገባው የሃብትና የሥልጣን ድርሻ ድርሻ አደላደል አንጂ፤ አለመግባባታቸው ምንጩና መነሻው።

የ Conflict አጥኚዎች ውዝግብ "ሁለት ወይም ከዚያ በለይ የሆኑት ወገኖች ተፃራሪ ሆነው የሚታዩ ዓላማዎች አንግበው አንዱ የሌላውን ዓላማ ግብ መምታት እንዳይሳካ የማድረግ ክንዋኔ ነው" ይሉናል። ሰዎች ሕይወታቸውን ሲመሩ የተለያዩ ግቦች አንገበው ይንቀሳቀሳሉ። በዚያኑ መጠን ተፃራሪ የሚመስሉ ፍላጎት፤ ዓላማ፤ ጥቅምና አመለካከቶች ያራምዳሉ። እነዚሁ ሌሎቹ ካነገቡትና ከሚያራምዱት ሳይጣጣሙና የተቃረኑ ሲመስላቸው ይጋጫሉ፤ ይሻኮታሉ፤ ይሯኮታሉ፤ ይቆራቆሳሉ። ባጭሩ ጠብ ይፈጥራሉ። ሁለቱም የራሳቸውን ዓላማ ለማሳካትና በዚያኛው መጠን የሌለኛውን ዓለማ ውድቅ ለማደረግ ይፍጨረጨራሉ። በዚያኑ ወቅት ዓላማዎቹ ተፃራሪ ስለሆኑ ወይም ለግብ አንጋቢዎቹ ስለሚመስላቸው የግድ ይፃረራሉ። ጎራ ይለያሉ። ደረጃው ይለያያል እንጂ ከቤተሰብ አለመግባባት እስከ የሶማሊያው ዓይነቱ አመሰቃቃይ እርስ በእርስ ጦርነትን የመሳሰሉ ቁሩቁሶች ሁላ በውዝግብ ውስጥ ይጠቃለላሉ፤ ለውዝግብ ተመራማሪዎቹ። ስለዚህ በቡደን ቡደን መቧደኑ አይደለም ወደ ግጭት የሚያመራቸው ተፃራሪ ወይም ተፃራሪ የሚመስላቸው

ግቦች ለመምታት ማለማቸው ነው እንጂ። መቧደን እየጠነከረ የሚመጣው ደግሞ በግለሰብ ደረጃ ሊጎናጸፏት ያልቻሉትን ሙብቶች በቡድንና በተደረጃ መልክ ለመጎናፀፍ እንደሚቀላቸው ባወቁ ቁጥር ባንድ ዓላማ ዙሪያ ለመደራጀት መበረታታቸውና መገፋፋታቸው ነው።

በዚሁ ምክኒያት በስብስቦች መካከል የተለያዩ የብሔርተኝነት ቅርፆች ከእነ መዘዞቻቸው ይከሰታሉ። ባህላችንና ሃይማኖታችን ሊጠፋ ነው ተብሎ በሚደረገው ቅስቀሳ የማንነት ፖሎቲካ ይበልጥኑ የሰው ልጅ ፈጠራ ገፅታው እየጎላ ሲመጣ እንመለከታለን። የብሔርተኛነት አስከፊ መግለጫዎችም አብሮ ይከሰታሉ።

በሃገራችን ኢትዮጵያም የምንመለከታቸው የብሔረሰብና የሃይማኖት አለመግባባቶች ሁላ ገዢው ፓርቲ የራሱን የሥልጣን ዕድሜ ለማራዘም ባለፉት 20 ዓመታት የተከተለውን ፖሊሲ ውጤት አድርገን የምንመለከተው ብዙዎች አለን። የተወሰነ እውነተኛነት አለው። በእርግጥም በተከተለው ፖሊሲ ቅርንጫፍ ማንነቶቻችን ቀዳሚ ሥፍራው ተቆናጥጠዋል። የዘር ፖሎቲካና የጎሣ ፌዴራሊዝም ብለን የምንሰይመው አካሄድ ውጤቶች ናቸው በከፊል። በእርግጠኛነት መናገር የሚቻለው ገዢው ፓርቲ ልዩነቶቻችን አለቅጥ አስፍቶዋል። የጋራ እሴቶቻችን አኮስሶዋል። የሚያለያዩን የማንነቶቻችን መግለጫዎች ሁላ አጋንነዋል። የምንጋራቸውን አሰባሳቢ ማንነቶቻችን ተድፍጥጠዋል። የጎሳ፤ የብሔረሰብና ያንድ እምነት አባልነታችን ገዝፎ እንዲጎላ ተደርጓል። ብሔራዊ አንደነታችን ስጋት ላይ መሆኑ አጠያያቂ አይደለም። የሕብተረሰቡ አገናኝ ጥልፍልፍ ሁላ እንዲበጣጠስ የተደረጉ ሙከራዎች አሉ። ይህ ሁሉ ደግሞ አንድ አናሳ ቡደን በሥልጣን ኮርቻ የማቆየት ዓላማ ያደረጉ ውጥኖች ናቸው። ሁሉም ኢትዮጵያዊ በሕገ መንግሥት የተካተተችው የመገንጠል ዋስትና የሚያሳሰበው ያለ ምክኒያት አይደለም።

ስለዚህ አንቅፅ 39 ከሕገ መንግሥቱ መሰረዝ ካለባቸው አንቀፆች ባንደኛ ደረጃ ማስቀመጡ አስፈላጊነት ዙሪያ መግባበት ላይ መደረሱ አስቸጋሪ የሚሆን አይመስልንም። በመድረክ የተሰባሰቡት የፖሎቲካ ድረጀቶች ያደረጉት ይህንኑ ይመስለኛል።

ያለፈው ታሪካችን የወደፊቱ አብሮነታችን አይታሰቤ አድርጎታል ባዩች በመካከላችን እስካሉ ድረስ አንደነታችን ዘላቂነቱ አስተማማኝ አይደለምና ያለፈው ታሪካችን አተራረክና አፃፃፍ ላይ መግባባት የግድ ይላል። የሚጠቅመው በቅርቡና በርቁ ታሪካችን ላይ የቋጠረነው አመለካከት፤ እሳቤና ግንዛቤና የጋራ አስተውሎት፤ አነባበባችን አዘራረፋችን በዛሬው ህልውናችን ብቻ ሳይሆን በመጪው እድላችን ላይ የማይናቅ አሻራ ማሳረፉ መቀበል ነው። ታሪካችን የወደፊቱ አብሮነታችን ግን አይታሳቤና አይሞኮሬ አድርጎታል የሚል አስተያየት ግን የለንም። የጋራ ትውስታችን ተዘክሮችን አካል አድረገነው ለአሳባሳቢው ማንነታችን አስተሳሳሪ ግብአት እናድረገው ብዮች ነን፤ ልክ ሌሎቹ እንዳደረጉት። ሌሎቹ እንዳወቁበት

እኛም እንወቅበት ነው መልእክቱ። በዜግነት ላይ የተመሰረተ አሳባሳቢ ማንነት በፅኑ መሰረቶች ለመገንባት ታጥቀን ተነስተናል እስካልን ደረስ።

በዜግነት ላይ የተመሰረተ፤ የሕግ በላይነት ያረጋገጠ የሙብት ዋስትና ነው የዚችን ሃገር ሕዝብ ልያቆራኘውና ልያስተሳስረው ብቃት አለው ብለን የሚናምነው። የአንድ ሃገር ልጅነታችን ላይ የተመሰረተ የዜግነት ሙብት መከበሩ፤ ከሁሉም በላይና በቅድሚያ።

ለረዥሙ አብሮነታችን ጠቃሚ ናቸው ብዬ ከምገምታቸው ወስጥ የሚከተሉት በሳቤ መወሰድ አለባቸው እላለሁ።

አሁን ሃገራችን የምትገኝበት ታሪክ መጋጠሚያ ላይ የተደቀኑብንን ፈታኝ ሆኔታዎች ባላፈው ታሪካችን ጠብ መነሻነት የሚነሱም ብቻ አይደሉም። በርካታ መስተካከል ያለባቸው ጉዳዩች አሉ። የብሔረሰቦችን አብሮነትን በተመለከተ።

1. ያልተማከለው የሥልጣንና ሃብት ክፍፍል በትክክል ያረጋገጠ ፌደራል ሥርዓት አማራጭነቱ ዘላቅነቱ ታምኖበት፤ በአከላሉም ሆነ በሥልጣን ድርሻ ድልድሉ መታረምና መሻሻል የሚገባቸውን እየተነቀሱ ማከል ያስፈልጋል።
2. አላስፈላጊ የሆነቸውን አንቅፅ 39 ከሕገመንግሥት ከነአካቴው ማስወጣቱ ላይ መስማማት የግድ ነው።
3. የሁለተኛው ቋንቋ አጠቃቀምና አስፈላጊነት ታምኖበት ወሳኔ ላይ መግባባት እስተረታጂካዊ ጥቅም ይኖሮዋል።
4.መንግሥትና ሃይማኖት ተቋማት በሕግና እወጃ ብቻ ሳይሆን በተግባርና በቅጡ መለያየታቸውን ማረጋገጥና ዜጎች ከሕግ ፊት እኩል የሚሆኑበትን አሠራራና አግባብ የማርጋገጥ ዋስትና ነው።
5.ከራሳችን ታሪክና አቻቻይ ከሆነው የእስልምና እምነትና አቻቻዩን አስተምህሮ ማጎልበቱ ሁለት እምነት ተካታዮች ጎን ለጎን ለሚኖሩበት ሃገራችን አማራጭ የማይገኝለት ምርጫ መሆኑን ግንዛቤ አስፈላጊነት።
ይህ በረዥሙና በስተራተጂካዊ ማግባባቶች በተመለከተ ሲሆን በሕዝባዊ እንቢተኛነት ያለውን ሥርዓት ማሽቀንጠሩ ተግበር በቁርጠኛነት ለመያያዝ የጋራ መታጊያ መድርኮች አስፈላጊነታቸው ታምኖበት እየተፈጠሩም እየተባዙ ናቸው። የሽግግር ጊዜን አስመልክቶ ታሪካዊ ስምምነት ይደረሳል ብዬ እገምታለሁ። ይህም ከዋና ዲሞክራሲያዊ ለውጥ ጋር ካልተቆራኘ ወደ የምንፈለገው መዳራሻ ግብ ማደረሱ አጠራጣሪ ነው። በአጭሩ ያለው ሥርዓት የማስወገዱ ተግባር ጎን ለጎን በቦታው የሚተካውን ሥርዓት አሰራር ላይ የጋራ መግባበት አስፈላጊነት አያጠያይቅም።

ዛሬ ይህንን እውን ለማድረግ በመጪዉፍ ላይ ባለው ትግል አዲስ ምዕራፍ ከፋች ዋዜማ ላይ እንገኛለን ብሎ አፍ ሞልቶ መናገር የሚቻል ይመስለናል። አንደኛው እምርታ ይህንን ሥርዓት አስወገዶ ተተኪው ላይ የጋራ መግባባትና ራዕይ ማስቀመጡ በትክክለኛ መስመር መጓዛችን ያመለክታል እላለሁ። በበኩሌ ከላይ በሰፊው እንደተመለከትነው እስካሁን ሲያወዛግበን ለነበሩ የአብሮነታችን ቀመር ላይ የጋራ መግባባት ዋዜማ ላይ እንገኛለን የሚል ግምት አለኝ። በዚሁ በትጋትና በፅናት ከገፋን ታሪካዊው አቻቻይ መፍትሔ ማገኘታችን አይቀሬ ነው።

ዛሬ የረዥሙ እስተራተጂ የትግሉ መደራሻ ግቦችም ላይም ሆነ በሥልጣን ያለውን መንግሥት በማስወገዱም ወይም ወደ ክብ ጠራጴዛ ቀርቦ ይህንኑ እንዲቀበል በሚደረገው ርብርቦች የተለያዩ ሃይሎች በጋራና ባንድ የመታጊያ መደረክ ዙሪያ ማሰባሰቡ ርብርቦሽ መጪዉፋቸው ከማንኛችንም የተሰወረ አይደለም። ወቅቱ በሰሜን አፍሪካ ከተቀጣጠለ መነሳሳቶች መማር የግድ ይላል። ከተሳኩትም ከተጨናገፉትም ትምህርት መቅሰሙ፤ በሊቢያና በየመን ሕዝባዊ መነሳሳቶች ዲሞክራሲያዊ ለውጡን የገቱና ያወሳሰቡ ኩነቶች ላለመደገም ከፍተኛ ጥንቃቄ ማሰፈለጉ ፍንትው ብሎ እየታዩን ናቸው። የአካባቢና የዓለማቀፍ ሃይሎች ጣልቃገበነት ምን ያህሉ የለውጥ ጉዞን እንደሚያወሳስቡ ተመልክተናል። ገዢ ሃይሎች ምን ያህሉ ሥልጣንን የሙጥኝ ብሎ ሂደቱን አሳቃቂ ከማድረግ እንደማይመለስ ምስክሮች ነን። ከራሳችን የ 1966 ቱ ሕዝባዊ መነሳሳትና፤ ከ 1997ቱ ተቀናጅቶ መታገል አሳፋሪው አጨራረስ መጠንቀቁም የግድ ነው። ከዚህ በፊት የተደረጉ ስህተቶችን መመርመር፤ የሥነልቦና የመንፈስ ዝግጅት በመለማመድ ላይ በምንገኝበት ባሁኑ ወቅት ተቀራርቦ መወያየቱ አማራጭ የለውም።

ለማጠቃለል፤ በዚሁ ወሳኝ ወቅት ከዚሁ አንጋፋው የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (እሕአፓ) መድረክ ሁሉም የራሱን ድርሻ እንዲወጣ የበኩሌን ጥሪዬን እያስተላለፍኩ ከዚህ በፊት በሕዝቡ እንደ ጣዖት ሲመለኩና ሲከበሩ የተመለከትናቸው የፖሎቲካ መሪዎች የዛሬው እጣፋንታ ልብ እንበል። ለተጣለባቸው እምነትና አደራ ብቁ ሆነው ባለመገኘታቸው ብቻ ሳይሆን ታሪካዊውና ወርቃማ እድል ደግመው ደጋመው አስመለጡብን ብሎ በመማረር ሕዝቡ ፊቱን እንዳዞረባቸው መገንዘቡ ጠቃሚ ነው እላለሁ። ሁሉም ታሪካዊና ትውልዳዊ ተልእኮውን ከታሪክ ፍርድ ነፃ በሚያወጣው መልኩ ይወጣዋል የሚል ፅኑ እምነት አለኝ። ሁሉ ከተልእኮው ከባድነትና ከተግዳሮቱ ተፈታታኝነት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የሃላፊነት ስሜት እንዳለው እርገጠኖች ነን። አንጋፋው ፓርቲያችሁ ከዚሁ በፊት በ1966 ካሳየው የዓላማ ፅናትና የመስዋዕትነት ዝግጁነት በተጨማሪ የፈጠራ ችሎታውና ተነሳሽነት መንፈሱን አድሶ ከሌሎች ጋር ለመሥራት ያላው በጎ ፍቃድ እንደሚያስመሰክር ቅንጣት ታህል ጥርጥር የለኝም። በተባበረው የኢትዮጵያ ሕዝብ አሸናፊነት ደግሞ ቅንጣት ታህል ጥርጥር የለኝም።

አመሰግናለሁ